የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ
ፓ ሪ ስ

Embassy of the Federal Democratic
Republic of Ethiopia
Paris

Date 27/03/2009 ዓ.ም.

N° ፈክፓ-0154-01/2/09.

# ለትውልደ ኢትዮጵያዊያን የውጭ አገር ዜጎች የወጣ ማስታወቂያ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5 ስር ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንደ አገር ውስጥ ባለሃብት መቆጠር ከፈለጉ በአገሪቱ የኢንቬስትመነት ህግ መሠረት ለአገር ውስጥ ባለሀብት በተፈቀዱ የኢንቨስትመንት መስኮች መሳተፍ እንደሚችሉ መገለጹ ይታወሳል።

ይሁን እንጂ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች በሚል ባወጣው ደንብ ቁጥር 270/3 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው ባለሀብቶች ብቻ የሚካሄዱ የስራ መስኮች ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው፡-

1. የባንክ፣ የኢንሹራንስ እና አነስተኛ የብድርና ቁጠባ ተቋም ሥራዎች፣
2. እቃዎችን የማሸግ፣ የማስተላለፍና የመርከብ ውክልና አገልግሎት፣
3. የብሮድካስቲንግ ሥራ
4. የመገናኛ ብዙሃን ስራዎች፣
5. የጥብቅና እና የህግ ማማከር አገልግሎት፣
6. አገር-በቀል ባህላዊ መድሃኒቶችን ማዘጋጀት፣
7. የማስታወቂያ፣ የፕሮሞሽን እና የትርጉም ሥራዎች፣
8. እስከ 50 መንገደኞችን የመጫን አቅም ባለው የአውሮፕላን የሚሰጥ የመንገደኞች አየር ትራንስፖርት

ስለሆነም ከላይ የተመለከቱት የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢትዮጵያዊ ዜግነት ላላቸው ብቻ የተፈቀደ መሆኑ ታውቆ፣ ትውለደ ኢትዮጵያዊ የውጭ አገር ዜጎች በአገር ቤት በኢንቨስትመንት ለመሳተፍ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

35, Avenue Charles Floquet - 75007 Paris - Tél. 01 47 83 83 95 - Télécopie 01 43 06 52 14